Free digital copy from ServeNow

# ስለ መንፈስ ቅዱስ ሊታወቁየሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች

ላርስ ዴንበርግ

ServeNow

Free digital copy from ServeNow

*ስለ አገልግሎት መርሆዎች ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች*

*The Basic Things You Need to Know About The Holy Spirit (Amharic)*

ላርስ ደንበርግ እና ቤን ፎሊ

አርታኢ፡ ዳና በርኪ

የቅጅ መብት © 2014 ሰርቭ ናው

በፈቃድ ጥቅም ላይ የዋለ፤ መብቱ የተጠበቀ

ISBN፡978-1-958730-42-3

የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከመጽሐፍ ቅዱስ አዲሱ መደበኛ ትርጉም ከማጥኛ ጽሑፍ ጋር፤ በቢብሊካ የታተመ ©1993፤2003

The Bible in Amharic©United Bible Societies 1962
Holy Bible, New Amharic Standard Version (አዲሱ መደበኛ ትርጉም).
Copyright © 2001 by Biblica, Inc.® በፈቃድ የተወሰደ: መብቱ በዓለም ዙሪያ የተጠበቀ ነው።

በሰርቭ ናው (*ServeNow*) የታተመ፣
1817 Austin Bluffs Parkway #110
Colorado Springs, CO. 80918, USA

Free digital copy from ServeNow

# ስለ መንፈስ ቅዱስ ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች

**መግቢያ**

በክርስቲያናዊ አኗኗርህ እርካታን አግኝተሃል ወይስ ተጨማሪ ራብ እና ጥማት አለህ? ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ መስተጋብርስ ረክተሃል? በቂ የሆነ የእግዚአብሔር ኃይል ወይም ሕልውና በሕይወትህ ውስጥ ይኖራል? ወይስ እነዚህና መሰል ጥያቄዎች አሉህ?

“ተጨማሪ ... ቢኖር ብዬ አስባለሁ”

“የጸሎት ሕይወቴ የበለጠ ስሜታዊ፣ ደግሞም ተለዋዋጭ እና የበለጠ በራስ የመተማመን ስሜት ያለው ሊሆን ይችላል ብዬ አስባለሁ።”

“በእርግጥ ጌታ በአስተሳሰቤ ሁሉ ውስጥ ቀዳሚ ሥፍራ አለው?”

የምናውቃቸው አያሌ አማኞች ዛሬ በሕይወታቸው ውስን ወይም ተለዋዋጭ ደስታ አላቸው። እስቲ ቀርበህ ጠይቃቸው። በእውነተኛ ስሜት ሳይሆን በሚፈጥሩት የቃላት ጋጋታ እና ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው የላይ ላይ ግንኙነት ጥልቅ የሆነ ደስታንና እርካታ የሞላበት ሕይወት ደግሞም ሰላምና መረጋጋትን ይሻሉ።

በጉባኤ ለአምልኮ እና ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ከመሰብሰብ፣ ሃይማኖታዊ ቃላትን ከመጠቀም፣ አሊያም የጸሎት መርሃ ግብሮች ላይ ከመሳተፍ የበለጠ በእምነት የሆነ ሕይወት አስፈላጊ ነው። ድንቅ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ ከእነዚህ ሁሉ የሚያልፍ ነገር በሕይወታችን ማድረግ

Free digital copy from ServeNow

ይፈልጋል፡፡ የሆነን ጠባሳ ሊያስወግድ ይሻል፤ የተሰባበሩ ስሜቶችን ሊጠጋግን ይፈልጋል፡፡ ደግሞም ብዙ መረዳቶች እንዲገለጡ መልካም ፈቃዱ ነው፡፡

ኤፌሶን 5:15-18 ላይ እንዲህ ተጽፏል፤ *እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ፤ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ። ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ። መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና።*

ስካርም ሆነ በመንፈስ መሞላት ሁለቱም በውስጣችን ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራሉ፤ አልኮል በደም ሥሮቻችን መንፈስም በልባችን፡፡ ከልክ ያለፈ አልኮል ልንቆጣጠረው ወደማንችለውና ምክንያታዊነት ወደ ጎደለው ባሕርይ ይመራል፡፡ የጠጣውንም ሰው በቅጽበት ወደ አውሬነት ይቀይራል፡፡ በአንጻሩ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ወደ መገራትና ምክንያታዊነት በመውሰድ ክርስቶስን ወደ መምሰል ይለውጣል፡፡

በሌሎች መናፍስትና በእግዚአብሔር መንፈስ ተጽእኖ ሥር የመሆን ወጤት ፍጹም የተለያየ ነው፡፡ የመጀመሪያው ወደ አውሬነት ሁለተኛው ደግሞ ክርስቶስን ወደ መምሰል ያመጣናል፡፡

## መንፈስ ቅዱስ ማነው?

ብዙ ወንጌላውያን አማኞች ኢየሱስ እና እግዚአብሔር አብ በመለኮት ሙላት ውስጥ ሁለት የተለያዩ አካላት እንደሆኑ ያምናሉ፡፡

ሆኖም ግን በመንፈስ ቅዱስ ማንነት ላይ ብዙ ግራ የሚያጋቡ እሳቤዎች ሲንጸባረቁ ኖረዋል፡፡ በተለያዩ ዘመናት በኖሩት አማኞች ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እንደ ቁስ እንጂ ሰብእና እንዳለው ተደርጎ አይታሰብም ነበር፡፡ ምንም ነገር

Free digital copy from ServeNow

ከእውነት ተፋልሶ መቀጠል አይችልም። መንፈስ ቅዱስ የሆነ የውሸት ኃይል ወይም የመንፈስ ዓይነት ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ ሁሉ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም የሥላሴ አካል ነው።

መንፈስ ቅዱስን ሰብእና እንዳለው የመለኮት አካል ስንረዳ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ ጋር እንዳለን ዓይነት ግንኙነት ከእርሱም ጋር ማዳበር እንጀምራለን።

## የመንፈስ ቅዱስ ባሕርያት

መንፈስ ቅዱስ ማሰብ ይችላል፤ *መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው* (1 ቆሮንቶስ 2:10)።

መንፈስ ቅዱስ አዋቂ ነው፤ *በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም* (1 ቆሮንቶስ 2:11)።

መንፈስ ቅዱስ ስሜት አለው፤ *ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ* (ኤፌሶን 4:30)።

*መንፈስ ቅዱስ ውሳኔ ይሰጣል፤ በእስያም ቃሉን እንዳይናገሩ መንፈስ ቅዱስ ስለ ከለከላቸው በፍርግያና በገላትያ አገር አለፉ* (የሐዋርያት ሥራ 16:6)።

መንፈስ ቅዱስ አእምሮ አለው፤ *ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና* (ሮሜ 8:27)።

መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ አለው፤ *በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር*

Free digital copy from ServeNow

*ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም* (1 ቆሮንቶስ 2:11)።

## በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ጉልህ ሚና አለው

አብዛኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በያዘው በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ የመጀመሪያው ገጽ ላይ መንፈስ ቅዱስ በግልጽ ተብራርቷል። *በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። ምድርም ባዶ ነበረች፣ አንዳችም አልነበረባትም፤ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር* (ዘፍጥረት 1:1-2 )።

## ቃሉና መንፈሱ

በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቃሉ ላይ ብቻ የሚያተኩሩና በሌላ ወገን መንፈሱ ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ሁለት የተለያዩ ጎራዎች ያሉ ይመስላል።

አንዱ ጎራ ቃሉ ላይ ትኩረት በማድረግና በማጥናት ብቻ ሙሉው እውነት ጋ እንደሚደረስ ያምናሉ። እነዚህ ሰዎች እውነትን ማወቅ ብቻውን በቂ መሆኑንና ይህም ከስሜት ጋር ምንም ተያያዥነት እንደሌለው አድርገው ሲቆጥሩ ሌላኛው ጎራ ግን የመንፈስ ቅዱስን አደራረግ ከሁሉም ነገር ጋር ያያይዛሉ።

በመንፈስ ቅዱስ ተግባራት ላይ ብቻ የሚያተኩሩት ግለሰቦች አንዳንድ ባሕርያትን እንደ መንፈሳዊነት ማረጋገጫ በማቅረብ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እሳቤ እንግዳ የሆነን ልምምድ በማስተማር ሲስቱ ይስተዋላል። ልምምዶቹንም የእግዚአብሔር መንፈስ በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሠራቸው ፍሬዎች እንደሆኑ አድርገው ይሞግታሉ።

ይህንን አግባብ ያልሆነና ክፉ አስተምህሮን የሚታዘቡ "የቃሉ ጎራዎች" "ከመንፈስ ቅዱስ የሆኑ ልምምዶችንና

Free digital copy from ServeNow

የመገለጫ መንገዶቹ ብዙም ስለማይመቹኝ ቃሉን ማጥናት ላይ ባተኩር ይሻለኛል!" ይላሉ።

ሆኖም ግን ጤናማ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ማድረግ የሚገባት በቃሉና በመንፈሱ በሆነ ልምምድ መካከል ያለውን ልዩነት ለማስወገድ ሁለቱን እኩል ጎን ለጎን ማስኬድ ነው። ሲጀመር ቃሉን ያደለን መንፈሱ ነው፡ *ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ* (2 ጴጥሮስ 1:20-21)።

በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ከዚሁ መንፈስ የሆነ እስትንፋስ አለበት፡- *የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል* (2 ጢሞቴዎስ 3:16)።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲናገር ቃሉን እንዲሰብክና እንዲያጠና እንጂ በኃይል ስለመሞላት ብቻ አልነበረም። *ቃሉን ስበክ፣ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፣ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ፣ ዝለፍና ገሥጽ ምከርም* (2 ጢሞቴዎስ 4:2)።

ቃሉና መንፈሱ እርስ በርስ ሲገፋፉ አይታይም። ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል መንፈሳዊ መነቃቃትንና ተሐድሶን መረዳት አይቻልም። ያለ እግዚአብሔር እውቀት ቃል ከእግዚአብሔር የሆነው ወይም ያልሆነው የትኛው እንደሆነ መለየት አይቻልም። መንፈሱ ከቃሉ የተዋሀዱ ስለሆነ በፍጹም አይለያዩ! ለእግዚአብሔር መንፈስ ተገቢ ሥፍራ የሌለው ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ውድ ሃብቱ ማድረግ እንዴት ይቻለዋል?

መንፈስ ቅዱስ ላይ ብቻ አትኩሮት የሚሰጡና የሽክርክሪት አሠራር ላይ የሚያውጠነጥኑ ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር

Free digital copy from ServeNow

ቃል እንደሚፈተሽ መረዳት አለባቸው። የእግዚአብሔር መንፈስ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አይቃረንም።

ከመንፈሱ ሕግ ይልቅ የሕጉ ፊደላት ላይ ያተኮሩ ፈሪሳዊያንን ኢየሱስ ሲገስጻቸው *እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው* ብሏቸዋል (ዮሐንስ 5:39) ።

ሮሜ 8:9 ላይ ጳውሎስ ሲጽፍ *እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም።* ብሎ ይናገራል።

## ቅዱሳት መጻሕፍት መንፈስ ቅዱስን በተለያዩ ምልክቶች ይመስሉታል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በብዙ ምልክቶች ተመስሏል።

### *ርግብ*

ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወረደበት። *የምወደው ልጄ እርሱ ነው እርሱን ስሙት …* የሚል ድምጽም ከሰማይ መጣ። በአጭሩ የመለኮትን ሙላ፤ አብ፣ ውልድና መንፈስ ቅዱስን በዚሁ ጥቅስ ውስጥ እናያለን።

### *የውኃ ጅረቶች*

የብሉይ ኪዳን ነቢያት እግዚአብሔር ለተጠሙት ሁሉ መንፈሱን እንደ ጅረት ውኃ እንደሚያፈስ ተናገሩ። ይህም በምድረ በዳ ዓለቱ በተመታ ጊዜ የውኃ ጅረቶች እንደጎረፉ ዓይነት የሚገልጽ ነው። ኢየሱስ ስለዚሁ እንዲህ ሲል ተናገረ *ከበዓሉም በታላቁ በኋለኛው ቀን ኢየሱስ ቆሞ እንዲህ ብሎ ጮኸ፡- “ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ።*

Free digital copy from ServeNow

*በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፣ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል።" ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ፤ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና* (ዮሐንስ 7:37-39)።

ኢየሱስ ስለዚህ ድንቅ ቃል ኪዳን ለሕዝቡ የተናገረው በኢየሩሳሌም በሚከበረው በዓል ላይ ታድሞ በነበረበት ወቅት ነበር። ሣምንቱን ሙሉ በሚከበረው በዚህ በዓል ላይ የሚታደሙት ሁሉ በነዚያ ጊዜያት የሚያስቡት ያኔ በምድረ በዳ የውኃ ጅረቶች ስላፈለቁበት ዓለት ነበር። ይህንንም መታሰቢያ የሚያደርጉት በከተማይቱ ዉኃ ተሸክመው በመዟዟር በመሰውያ ላይ እያፈሰሱ ከብሉይ ኪዳንም በመጥቀስ እየዘመሩ ነበር። *ውኃውንም ከመድኃኒት ምንጮች በደስታ ትቀዳላችሁ* (ኢሳይያስ 12:3)። ኢየሱስም በድንገት ቆሞ ያ ዓለት እኔ ነኝ ብሎ ገለጸ፣ *ይህንንም ስለመንፈስ ቅዱስ ተናገረ።*

ዛሬ ኢየሱስ በሰማያት በአብ ቀኝ ተቀምጦ የውስጥ ጥልቅ ጥማታችንን በመንፈሱ ማርካት ይችላል። የራሳችንና ወደኛ የሚመጡትን ሰዎች ጥማት የሚያረካ በእኛ ላይ የሚፈሰው ዉኃ እርሱ ነው።

## *እሳት*

በበዓለ ሃምሳ ቀን እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው በአንድ ሥፍራ ለጸሎት በተሰበሰቡ ደቀ መዛሙርት በእያንዳንዳቸውም ላይ በእሳት መልክ ተቀመጡባቸው። *በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፣ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር* (የዋርያት ሥራ 2:4)።

በጨለማ ለተዋጠ ክፍል እሳት ብርሃን ይሆናል፣ ያጠራል፣ ያቃጥላል፣ ኃይልና ሙቀትንም ይሰጣል። የእግዚአብሔር መንፈስ እሳትም ከሕይወታችን ላይ ገለባን በማቃጠል

Free digital copy from ServeNow

ያጠራናል፣ ከውስጣችን ይደምቃል፣ የእግዚአብሔርንም ሙቀት እያካፈለን ለውስጥ ማንነታችን የእውነቱን አብርሆት ይሰጣል።

***ነፋስ***

ስለ መንፈስ ቅዱስ በነፋስ አምሳልም ተነግሯል። መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስን ለመግለጽ የተጠቀማቸው አገላለጾች ልክ ፊኛ በኃይል በሆነ ሁኔታ በአየር ሲሞላ እንዳለው ዓይነት ወይም ሻማ ለማጥፋት እንደምንጠቀመው የትንፋሽ ጉልበት ነው። ደግሞም በሩጫ ወቅት በሚደረግ የአተነፋፈስ ጉልበትም ይመሰላል። አንዳንዴ በቃላት ለመግለጽ የምንቸገረውና ነፋስ ሲነፍስ እና በኃይል ሲያፏጭ ደግሞም እየሰባበረ መንገዱን እንደሚያበጃጀው አልፎም ታላቅና አስገራሚ የሆነውን ኃይሉን እንደሚገልጥ ብርቱ ነፋስ መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ ነው። የመንፈስ ጉልበት በሁለቱም መካከል ያለውን ወይም በሁለቱም ጫፎች ላይ ያለውን ቅርጽ ይወስዳል። መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚኖር የእግዚአብሔር ኃይል ነው።

ላልበሰለው የሕይወታችን ሽክላ ቅርጽ እንዲሰጠውና ክርስቶስን ወደሚመስል ቅዱስ ፍቅር፣ የቅድስና ኑሮ፣ ንጽሕና እና ለሰዎች ሁሉ ወደመራራት ቅርጽ እንዲያመጣው ጌታችን የሆነው መንፈስ ቅዱስን ልናከብረውና ልንታዘዘው ያስፈልጋል።

ከብሉይ ኪዳኑ የሕዝቅኤል መጽሐፍ ምዕራፍ 37 በሸለቆ ስለተጣሉ ደረቅ አጥንቶች እናነባለን። ነቢዩ ትንቢት ሲናገር አጥንቶቹ መገጣጠም ቢጀምሩም ትንፋሽ አልነበረባቸውም። የእግዚአብሔርም ነፋስ መጥቶ ሕይወትን ሰጣቸው። እግዚአብሔርም ነቢዩን አለው መንፈሴንም በውስጣችሁ አሳድራለሁ … (ሕዝቅኤል 37:14)።

Free digital copy from ServeNow

በእኛ ውስጥ ያለውን አዲስ ሕይወት ኢየሱስ በነፋስ ይመስለው ነበር። ይህም የማይገታ የነጻነት ሕይወት ምልክት ሲሆን ብናፍነው እንኳ በቀላሉ የሚሞት ነፋስ መሆኑን አስረድቷል። ኒቆዲሞስ በሌሊት ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተናገረው *ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፣ ድምፁንም ትሰማለህ፣ ነገር ግን ከወዴት እንደ መጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው* (ዮሐንስ 3:8)።

## *ዘይት*

ዘይት የመንፈስ ቅዱስ ተምሳሌት ሲሆን እኛ በተለምዶ ከፈውስ፣ ለአገልግሎት መለየት ወይም መጠራት ጋር ስናያይዝ ቆይተናል። በመንፈሱ በኩል ለተለየ ሥራ ተቀብተን ለጌታ እንደሚሆኑ ደግሞም የተለዩ ቅዱሳን ተደርገናል።

## *ማኅተም*

መንፈስ ቅዱስ የባለቤትነት ማረጋገጫ ማሳያ በሆነው በማኅተም ይመሰላል። በውስጣችን ያለው የመንፈስ ምስክርነት የጌታ መሆናችንን ያረጋግጣል። *እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል፣ ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል፣ ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፣ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ* (ኤፌሶን 1:13)።

## *ሌሎች መጠሪያዎች*

መንፈስ ቅዱስ በሌሎች ብዙ ስሞች ይጠራል፡- የፍቅር መንፈስ፣ የኃይል መንፈስ፣ ቅዱስ መንፈስ፣ የእውነት መንፈስ፣ የክብር መንፈስ፣ ረዳት፣ የጸጋ መንፈስ፣ የልመና መንፈስ እና የመሳሰሉ ናቸው።

Free digital copy from ServeNow

## የመንፈስ ቅዱስ ተግባር ምንድነው?

### *የመንፈስ ቅዱስ ተግባር መውቀስ ነው።*

የመንፈስ ቅዱስ አንዱ ተግባር ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅና እና ፍርድ መውቀስ ነው። 1 ዮሐንስ 3፡4 እንደሚናገረው ኃጢአት ማለት የሆነን ቋሚ ምልክት እንደማጣት ነው። የኢላማ ልምምድ አድርገህ ታውቅ ከሆነ ኢላማውን በግማሽ ሜትር፣ ግማሽ ሜዳ ወይም ግማሽ ኪሎ ሜትር ብትስት ያው ሳትክ ነው። የምንለካው ምን ያክል መጥፎ እንደሆንን ሳይሆን ምን ያክል መልካም እንዳልሆንን ነው። ኃጢአት ኢላማን መሳት ከሆነ ኃጢአት ፍጹም አይደለም - ኢላማው ግን ፍጹም ነው።

ኢየሱስን ያደምጡት የነበሩትን ፈሪሳዊያንን መንፈስ ቅዱስ ሲወቅሳቸው ከኢላማው ምን ያክል ርቀው እንደነበር ይረዱ ጀመር። *"ለቀደሙት፦ 'አትግደል፡' እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ 'የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል እኔ ግን እላችኋለሁ፣ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም፦ 'ጨርቃም' የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ 'ደንቆሮ' የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል '*(ማቴዎስ 5:21_22)። *"'አታመንዝር' እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል* (ማቴዎስ 5:27-28)።

ይህ መልካም ዜና ነው? ግፊቶቻችንን መቆጣጠር ለማንችል ለእኛ በጣም ከባድ ነው። አሁን ስለነዚህ ማሰብ እንኳ አንችልም!

እግዚአብሔር እንድንሆንለት የሚፈልገው ዓይነት ሰዎች በታማኝነት መሆን እስክንጀምር ድረስ እራሳችንን እያታለልን እንኖራለን። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ቀረብ ብሎ ወደ ኃጢአታችንና ወደ ጽድቁ እየጠቆመ ያሳየናል።

Free digital copy from ServeNow

የሕዝቅኤል መጽሐፍ እንዲህ ይገልጻል፣ *መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ በትእዛዜም አስሄዳችኋለሁ፥ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ ታደርጉትማላችሁ* (ሕዝቅኤል 36:27)።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ትእዛዝ የነበረው በአዲሱ ኪዳን ዘመን ደግሞ ተስፋ ሆኗል። ኢየሱስ መምህራችን ብቻ አይደለም ሕይወታችንም ጭምር እንጂ።

*እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና* (ሮሜ 8:1)።

*እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን...* (2 ቆሮንቶስ 3:18) ።

## ***የመንፈስ ቅዱስ ተግባር አማኞችን ማተም ነው።***

በጥንት ዘመን ለሆነ ድርጅት የአገልግሎት ክፍያ ስትከፍል የደረሰኝህ ቅጅ ላይ ድርጅቱ ማኅተም ያሰርፍበታል። በጭሩ ማኅተሙ "ሙሉ በሙሉ ተከፍሏል" የሚል ነው። ለከፈልከው ገንዘብም ደረሰኙን ይሰጡሃል። መንፈስ ቅዱስ ማኅተማችን ደረሰኛችንም ነው።

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር እንደሆንን ማረጋገጫችን ነው። *እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል፣ ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል፣ ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፣ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ* (ኤፌሶን 1:13)።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ብዙ አስፈሪ ውጊያዎች ተካሂደዋል። ወታደሮችም ቁልፍና ስልታዊ ሥፍራዎችን ለመቆጣጠር ደጋግመው ሞክረዋል። ተዋግተው ሰፊ ቦታ ለመያዝና መሐንዲሶችም ከኋላቸው መጥተው ድልድዮችን

Free digital copy from ServeNow

እንዲገነቡ በውጤቱም ብዙ ወታደሮችን ማጓጓዝ እንዲችሉ በእግሮቻቸው ወንዞችን ተሻግረው የተኩስ ናዳዎችን አዝንበዋል። ይህም የአያሌ ሰዎችን ነፍስ አጥፍቷል፤ ይህ ነው የማይባል የጦር መሣሪያዎችንና ንብረቶችንም አውድሟል። በሕይወታችን ውስጥ ክርስቶስ ወሳኙን ሥፍራ የተቆጣጠረው ያለጦርነት አይደለም። በቀራኒዮ የደሙን ሕይወት አሳልፎ በመስጠት ኃጢአታችንን በሙሉ በትከሻው ወስዶ በኛም ምትክ ሞቷል። መንፈስ ቅዱስም በበዓለ ሃምሳ ቀን በእሳት አምሣል የክርስቶስን ሥራ አረጋግጧል። በደሙና በእሳት የተዋጀን ነን።

## ***የመንፈስ ቅዱስ ተግባር ሁሉን ነገር እኛን ማስተማር ነው።***

*አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል* (ዮሐንስ 14:26)።

ሁሉን ነገር ታውቃለህ? አይመስለኝም! መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን አዋቂ ብቻ ሳይሆን በኢየሱስ ጉዳይ ላይ የተጠበበ ነው። ኢየሱስን በኛ ውስጥ ሊያከብር ወደኛ መጥቷል።

## ***የመንፈስ ቅዱስ ተግባር ኢየሱስ ያስተማረንን በሙሉ ማሳሰብ ነው፡፡***

ኢየሱስ ስለ ምን አስተማረን? አባቱንና እርስ በርሳችን እንድንዋደድ አስተምሮናል። በቀራንዮ ከወንበዴዎች ጋር እንኳ የሚሞትበትን ሥፍራ በመጋራት ለሌሎች ያለውን ፍቅር በግልጽ አሳይቷል።

## ***የመንፈስ ቅዱስ ተግባር አጽናኝ፣ ረዳትና አሠልጣኝነት ነው።***

ወዴት መሄድ እንደሚገባን የማናውቅበት ጊዜ ይኖራል። ሕመማችን ከአቅም በላይ፣ ሸክማችን ከባድ፣ እንዲሁም

Free digital copy from ServeNow

መንፈሳዊ መረጋጋትን የሚያመነጩ ዕጢዎቻችንም ሥራ የሚያቆሙ ሰዎች ነን። እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ሊያጽናናን፣ ሊረዳን፣ የትኛውንም ተግዳሮት መቋቋም እንድንችል ካሁን ቀደም ያልተለማመድነውን የመንፈስን ኃይል ሊያስታጥቀን አብሮን አለ።

## *መንፈስ ቅዱስ ትልቁ የኢየሱስ ስጦታ ነው።*

ከመስቀል አስቀድሞ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ አንድን ታላቅ ተስፋ ሰጣቸው። *እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ።* (ዮሐንስ 14: 16-17)።

*እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ* (ዮሐንስ 16:7)።

ይህ የደቀ መዛሙርት ካሳ አልነበረም። አጽናኙ ከኢየሱስ የተሰጣቸው ስጦታ ነበር። ዛሬም ይህ ስጦታ በነጻ ለኛም ተሰጥቶናል። ቅዱሳት መጻሕፍትም *መንፈስ ይሙላባችሁ* ብለው ያዝዙናል። ልንታዘዘው የማንችለው ቢሆን ኖሮ ትእዛዙ ተገቢ ባልሆነም ነበር።

## የሚከብደው ምኑ ነው?

አንዳንድ የሥነ መለኮት ምሁራን የመንፈስ ቅዱስን ተግባራትና መገኘቱ ከቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና በኋላ እንደ ቀድሞው ዘመን አስፈላጊ አይደለም በማለት ይሞግታሉ። ነገር ግን በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ተግባራት ውስንነትና ሁለንተናዊ መገኘቱ ድሮ የቀረ እንደሆነ አልተጻፈም። በጭንቀት ለነበሩት ለእነዚያ ተከታዮቹ ለልዩ ልዩ የመለኮት መገለጫ አቅጣጫዎች ተስፋን

Free digital copy from ServeNow

የሰጠው ያው መንፈስ በዚህ ዘመን ላለነው ሁላችንም ያንኑ ሊተገብር በውስጣችን መኖሪያውን አድርጓል።

አንዳንድ ጊዜ ያልታወቀውንና ያልታየውን የወደፊቱን እንፈራለን። ስለ ነገዎቻችን እርግጠኞች መሆን እንፈልጋለን። ስለማናውቀው ነገር ከማጥናት አሊያም አለመታዘዝን ስንመርጥ ለመንፈሳዊነት የወገንን መስለን የተቃዉሞ ካባችንን እንደርባለን። ይህም አንድ ዋጋው ውድ የሆነን ደግሞም የመግዛት አቅም የሌለንን ዕቃ በየመደብሩ እንደመመልከት ነው። የተለጠፈበትን ዋጋ እስክናይ ድረስ ገዝተን የግላችን ለማድረግ እንጓጓለን። ሌሎች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልተው ተነቃቅተው ስናይ “ጌታ ሆይ መንፈስህን በዚህ መልኩ በሰዎች ላይ ማፍሰስህ መልካም ነገር ነው… ነገር ግን በወንዶችና ሴቶች ልጆቼ ላይ አይሁን” ማለት ይቃጣናል።

መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ ስላለው ኃጢአት ሲገዳደረን ክፍት ካልሆንለት ለመሥራት ይቸገራል። ምንም እንኳ ኃጢአታችንን መናዘዝ ከባድ ቢሆንም እንጋፈጠው!

ለመናዘዝ ፈቃደኞች ስንሆን እንኳ ከሚገባው በላይ ላለመናዘዝ እየፈራን በቁጥብነት፣ በኩራት እና በቂም እንናገራለን። ያውም ኑዛዜአችንን በፈቃደኝነት ከልባችን እንደማፍሰስ ፈንታ ለሚወጋጋን ህሊናችን ስንል ብቻ ለግብር ይውጣ የኑዛዜ ቃሎቻችንን እናነበንባለን።

አንድን ሰው እንደበድልን ስናውቅ ከሰውዬው ጋር ግጭት ውስጥ እንዳንገባ ለማስመሰል የማንፈነቅለው ድንጋይ አይኖርም። ብንናዘዝ እንኳ ልክ ሕጻናት ይቅርታ እንዲጠይቁ ሲታዘዙ በቂም “አሁንስ ደስ አለህ?” በሚል ስሜት በአስቸጋሪ ሁኔታ እንደሚያደርጉ እንሆናለን። እግዚአብሔር ግን እንደዚህ ባለ ሁኔታ አይረካም። በመንፈሱ ኃይል እንድንሰበር ይሻል። በፊቱ ትኑታን እንጂ

Free digital copy from ServeNow

ኩራተኞች እንድንሆን አይሻም። *ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፣ራሱንም የሚያዋርድ ከፍ ይላል* (ሉቃስ 14:11)።

አእምሮአችን ከመንግሥቱ አጀንዳ ውጭ በሆኑ ሌሎች ነገሮች የተቅበዘበዘ ከሆነ እግዚአብሔር በውስጥ ማንነታችን ሥፍራ ለማግኘት በጣም ይቸገራል። እንዲህ ባለ ወቅት “መንፈስህን እንደገና በላያችን አፍስስ” ብለን መጠየቅ መጀመር አለብን።

## የመንፈሱ በውስጣችን የመሥራት ውጤት ምንድነው?

መንፈስ ቅዱስ ክፍት ስንሆንለትና ስንገኝለት መንፈሳዊ ሕይወታችን ይደርቃል? ይደነዝዛል? በፍጹም! የሚከተሉትን በሕይወታችን መለማመድ እንጀምራለን፡

### *በመንፈስ ፍሬ በኩል አዲስ ባሕርይ*

መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ሕይወት የታዩት ባሕርያትን በሙሉ በኛም ሕይወት ይደግማል። የመንፈስ ፍሬ ምንድነው? ገላትያ 5፡22-25 ላይ የተሰጠውን ማብራርያ በጥንቃቄ አንብበህ እነዚህ ባሕርያት በኢየሱስ ሕይወት ውስጥ እንዴት እንደተገለጡ አስብ። *የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም። የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ። በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ* (ገላትያ 5:22-25)።

### *በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አማካኝነት ጠቃሚዎች መሆን*

ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን እንዲሆን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ተሰፋ አለን። እነዚህ ስጦታዎች ምን ምንድናቸው?

Free digital copy from ServeNow

በመጽሐፍ ቅዱሳችን በአራት የተለያዩ ምንባቦች ውስጥ ተዘርዝረዋል። የሚከተሉት ናቸው።

*እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤ ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር፤ አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤ የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፤ የሚገዛ በትጋት ይግዛ፤ የሚምር በደስታ ይማር* (ሮሜ 12:6-8)።

*የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።*

*ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል። ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት፥ ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ፣ ለአንዱም ተአምራትን ማድረግ፣ ለአንዱም ትንቢትን መናገር፣ ለአንዱም መናፍስትን መለየት፣ ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፣ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል፤ ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና፣ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር ይሰጠዋል፣ ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል። እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን፣ ሁለተኛም ነቢያትን፣ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፣ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፣ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፣ እርዳታንም፣ አገዛዝንም፣ የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጎአል። ሁሉ ሐዋርያት ናቸውን? ሁሉስ ነቢያት ናቸውን? ሁሉስ አስተማሪዎች ናቸውን? ሁሉስ ተአምራትን ይሠራሉን? ሁሉስ የመፈወስ ስጦታ አላቸውን? ሁሉስ በልሳኖች ይናገራሉን? ሁሉስ ይተረጉማሉን? ነገር ግን የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ*

Free digital copy from ServeNow

*ፈልጉ። ደግሞም ከሁሉ የሚበልጥ መንገድ አሳያችኋለሁ* (1 ቆሮንቶስ 12:4-11፤ 12:28-31)።

*ነገር ግን እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን። ስለዚህ፦ "ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ፡ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ፡" ይላል። ወደ ምድር ታችኛ ክፍል ደግሞ ወረደ ማለት ካልሆነ፣ ይህ ወጣ ማለትስ ምን ማለት ነው? ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው። እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ ሌሎቹም ነቢያት፣ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፣ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፣ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፣ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፣ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ* (ኤፌሶን 4:7-13)።

*ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፣ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ* (1 ጴጥሮስ 4:10)።

በ1 ቆሮንቶስ 12 ላይ እንደተጠቀሰው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ለእግዚአብሔር ሕዝብ ለጋራ ጥቅም እንደሚሰጡ ይናገራል። ቁጥር 11 ላይ እንደሚታየው መንፈሱ ስጦታዎቹን እንደፈቀደ ለሰዎች ይሰጣል። ኤፌሶን 4፡12 ላይ በግልጽ እንደሚታየው እነዚህ ስጦታዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልግሎት ለማዘጋጀት የክርስቶስንም አካል ለማነጽ ነው። በብዛቱ ላይ የተለያዩ አስተያየቶች ቢኖሩም መጽሐፍ ቅዱስ ግን ስጦታዎቹ ልዩ ልዩ መሆናቸውን ይናገራል።

ኢየሱስ በምሳሌ ሲያስተምር እንዲነግዱበት ለአንዱ አምስት፣ ለሁለተኛው ሁለት እንዲሁም ለሌላኛው አንድ መክሊት እንደተሰጣቸው እግዚአብሔርም መስጠት

Free digital copy from ServeNow

ባሕርይው በመሆኑ እነዚህን ስጦታዎች እንደወደደ ለሰዎች ያከፋፍላል። *በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን፣ የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ፣ እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፣ እርስ በርሳችንም አንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን። እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤ ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር* (ሮሜ 12:4-6)።

እነዚህ ስጦታዎች በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በማኅበረሰብ ውስጥ በተለያየ መልኩ እንድናገለግል ያደርጉናል። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ መንፈሱ ሲፈስ ልዩ ልዩ ስጦታዎች ተሰጥተው በሥራ ላይ እንደነበሩ አስታውስ።

## *መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ክብር ፊት አምልኮን በፍርሃት እንድናቀርብ ያነሳሳናል።*

የእግዚአብሔር መንፈስ ሲንቀሳቀስ ሕዝቡ እግዚአብሔር አብን፣ እግዚአብሔር ወልድንና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ለማምለክ ይነቃቃል። በበዓለ ሃምሳ ቀን የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ የመጀመሪያ ተግባሩ በሰዎች ሕይወት ውስጥ የአምልኮ ፍንዳታ ማድረግ ነበር። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ክብር ሲገልጥ በሚያስደንቅ ሁኔታ መፈራቱንም ያመጣል።

## *ለምሳሌ ሐዋርያው ዮሐንስ በኢየሱስ ቅዱስ ግርማ ትጥቅ ፈትቶ እንደ ሞተ ሰው ሆኖ ወደቀ።*

መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ያድሳል።

አብዛኛውን ጊዜ ከዮሐንስ ራእይ ተደጋግሞ የሚጠቀሰው ክፍል ከፍቅር ጋር የተያያዘ ነው። በኤፌሶን ላለችው ቤተ ክርስቲያን እንዲህ አለ፤ *ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፡ -የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና* (ራእይ 2:4)። በሎዶቅያ ላለችውም ሲናገር *እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው* (ራእይ 3:16) ይላታል።

Free digital copy from ServeNow

መንፈስ ቅዱስ ሁለቱንም ችግሮች ይፈታል። በኢየሱስ ፍቅር ደጋግመው እንደሚወድቁ የብዙ ሰዎችን ምስክርነት በተደጋጋሚ እሰማለሁ። መንፈሱ ለእግዚአብሔር ፍቅር እንድንገዛና ንቁ ደቀ መዛሙርት በመሆን ለመታዘዝ ያለንን ፍላጎት እንደገና ያቀጣጥላል።

## *መንፈስ ቅዱስ የእግዚኣብሔርን ኃይል ይገልጣል።*

መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ፍሬ ያዘጋጃል። *የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም* (ገላትያ 5:22-23)። ደግሞም በኃይል ሊያስታጥቀን ተስፋ ሰጥቶናል።

ይህ አእምሮአዊ ጽንሰ አሳብ ብቻ ሳይሆን ጠንከር ያለ እውነታ ነው። ጳውሎስ ስለ ስብከቶቹ ሲጽፍ ያ ኃይል ምን እንደሆነ እንዲህ ያስረዳል፤ *ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበረ እንጂ፣ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም* (1 ቆሮንቶስ 2:4)። ስለዚህ ኃይል ቤተ ክርስቲያኒቱ አንዳች ነገር እንድታውቅ ፈልጎ ነበር። *ይኸውም እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ ላይ እንዳይመሠረት ነው* (1ቆሮንቶስ 4፡5)።

*ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን* (2 ቆሮንቶስ 4:7)።

በኤፌሶን የሚገኙ አማኞችም በዚህ ኃይል ላይ እንዲደገፉ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ያበረታታቸዋል፤ *በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ* (ኤፌሶን 6:10)።

በተመሣሣይ መልኩ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክት ያ በእግዚአብሔር የተሰጠው መንፈስ ኃይለኛ መሆኑን አስረድቶታል። *እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር*

Free digital copy from ServeNow

*ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና* (2 ጢሞቴዎስ 1:7)።

እንደሚለሰበቸ መንፈሱ በላያችን ሲፈስ ዳግም የእግዚአብሔርን ኃይል እናውቃለን።

## *መንፈስ ቅዱስ እንድንጸልይ ይረዳናል።*

ስለ ጸሎት ስናስብ አንዳንዴ የምንናገረው ይጠፋብናል። ለጸሎት በፊቱ ቀርበን ባዶ ቃላትን ወይም የገና የምኞት ዝርዝራችንን እግዚአብሔር ማድመጥ አይፈልግም። መንፈሱ በሕይወታችን በሙላት ሲኖር በውስጥ ማንነታችን የሚፈጠረውን መሻት እግዚአብሔር ሊያደምጠው በሚወደው መልኩ እንድንጸልይ ያግዘናል። *እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፣ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤ ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና* (ሮሜ 8:26-27)።

ለእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት ክፍት የሆኑት አብያተ ክርስቲያናት የጸሎት ስብሰባዎቻቸው ለልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎቶችና የወንጌል ሥርጭት እንደ ኃይል ማዕከል ነው።

## *መንፈስ ቅዱስ ወንጌልን ለመስበክ ድፍረት ይሰጠናል።*

ከበዓለ ሃምሳ በፊት ስለ እምነታቸው ምንም ኃይል ያልነበራቸው ደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስ በኃይል ከወረደባቸው በኋላ አስደናቂ የሆነ ለውጥ ታይቶባቸዋል። ኢየሱስን ሦስት ጊዜ ክዶ የነበረው ጴጥሮስ በዚሁ ዕለት በመንፈስ ቅዱስ ተነክቶ በአይሁዳዊያን ፊት በመቆም ኢየሱስን በኃይል ሰበከ። በኋላም በካህናትና አለቆች ፊት በመንፈስ ቅዱስ በሆነለት ድፍረት ተነሥቶ ቆሞ እንዲህ አለ፤ *በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ*

Free digital copy from ServeNow

*እንዲህ አላቸው፡- "እናንተ የሕዝብ አለቆችና ሽማግሌዎች፣ እኛ ዛሬ ለድውዩ ሰው ስለ ተደረገው መልካም ሥራ ይህ በምን እንደዳነ ብንመረመር፣ እናንተ በሰቀላችሁት እግዚአብሔርም ከሙታን ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህ ደኅና ሆኖ በፊታችሁ እንደ ቆመ፣ ለእናንተ ለሁላችሁ ለእስራኤልም ሕዝብ ሁሉ የታወቀ ይሁን* (የሐዋርያት ሥራ 4:8-10)።

## *መንፈስ ቅዱስ በዙሪያችን ላሉት ሁሉ ልዩ ፍቅር እንዲኖረን ያደርገናል።*

የቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ለጸሎት ሲሰበሰቡ ወንጌል እንደ ምስጢር የሚያዝ ነገር አልነበረም። ወንጌል ለሌሎች የሚያጋሩት ዐቢይ ጉዳያቸው ነበር። በዙሪያችን ሆነው ወንጌል ላልሰሙ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ እንድናዝንላቸው ያደርገናል፤ ትኩረቱም የጠበበ አይደለም። እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ ወዷልና። በአንጾኪያ ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስና በርናባስ ለተመረጡት ሥራ ወጥተው ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ እንዲሠሩ መንፈስ ቅዱስ ተናገሯቸዋል።

ዛሬም የመንፈስ ቅዱስ ታላቅ እንቅስቃሴ ቤተ ክርስቲያንን ይልካታል። በአውሮፓ፣ ስካንድኔቪያ፣ አሜሪካና ካናዳ ውስጥ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ዓለምን በወንጌል የመድረስ መነሣሣታቸው ቢቆምም እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በላቲን አሜሪካ፣ እስያና አፍሪካ ውስጥ ያሉት አብያተ ክርስቲያናትን ቀስቅሷል።

## *መንፈስ ቅዱስ ለድሆች ርኅራኄ እንዲኖረን ያነሣሣናል።*

ኢየሱስ የመጀመሪያ የጀማ አገልግሎቱን በይፋ ሲጀምር ለድሆች የማዘንን ጉዳይ በግልጽ ተናግሯል። *የነቢዩንም የኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጡት፣ መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ፦ " 'የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ*

Free digital copy from ServeNow

*ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፣የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል ...”* (ሉቃስ 4:18)።

እግዚአብሔር የድሆች ጠበቃ ነው። በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ በነቢያት በኩል ሕዝቡን ሲያጽናና ፍቅርንና ፍትሕን መውደድ ብቻ ሳይሆን ለድሆች ማዘንን ጭምር ተናግሯቸዋል። ኢየሱስም በዚሁ የመልእክት ይዘት አገልግሎቱን ቀጠለ።

በዚህ ምዕተ-ዓመት ውስጥ ማኅበራዊ ተግባራት ሃይማኖታዊ ገጽታ እንዳለው እንደ ‘ኮሚኒዝም’ አድርገን እናስባለን። ለድሆች ማሰብ ግን ቢያንስ የ3,000 ዓመታት የዕድሜ ባለጠጋ ነው። ምንጩም ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

የእግዚአብሔር መንፈስ ለወንጌል አዋጅ ነጋሪነት አስታጥቆ ሠራተኞቹን ሲልክ ለድሆች ማሰብንም በተመሣሣይ መልኩ እንዲሠሩበት ይፈልጋል።

ለመበለቶችና ሕጻናት እንክብካቤ በማድረግ በዓለም ሁሉ ዙሪያ ወንጌል የተሰራጨበት አሠራር ነበር። ባለፉት ዘመናት የእግዚአብሔር መንፈስ መልእክተኞችን በምሪት ለወንጌል ሥራ ወደላከባቸው ሥፍራዎች ሁሉ የትምህርት ተቋማት፣ ሆስፒታሎችና ክሊኒኮች ጎን ለጎን ተስፋፍተዋል።

## *መንፈስ ቅዱስ እርስ በርሳችን መካከል ያለውን ፍቅር ያበዛል።*

ሁሉንም ሰው መውደድ ቀላል አይሆንም። እንዲያውም አንዳንዶቹ አብሮ ለመኖር አስቸጋሪ ናቸው። ሆኖም ግን መንፈስ ቅዱስ የምናገኛቸውን ሰዎች ሁሉ መውደድ የምንችልበትን ተስፋ ሰጥቶናል። አንዳንድ ቁስሎቻችንን የምክር አገልግሎትም ሆነ የሥነ ልቦና

Free digital copy from ServeNow

እውቀት ሊያስወግዳቸው አይችልም። ነገር ግን ፍቅር የሆነ የእግዚአብሔር መንፈስ የተሰበረውን የሰዎችን ግንኙነት መጠገን ይችላል።

## ***የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ወደ ተቃውሞና ስደት ይመራል።***

የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲመራህ በፈቀድክለት ልክ ወደ ሚቃወሙህም ጭምር ደጋግሞ ይሰድሃል። ጳውሎስ ተራና ሞኝ ተብሎ ነበር። ደግሞም ምስክርነቱን ያቀረበለት አገረ ገዢው ፊስጦስ “ጳውሎስ ሆይ አብደሃል!” ብሎ እንደጮኸ አንብበናል። የቀደሙት አማኞች በፍቅር የሆነ ኅብረት ቢያደርጉም በስደት ምክንያት ግን ተበታትነዋል።

ከባላጋራህ ጋር በብዙ የተለያዩ ከባባድ ግጭቶች ውስጥ ትገባለህ። ለብ ካሉት አማኞች ጋር ምንም ጉዳይ የለውም። አንተ ዘወትር ለጌታ ከተቀጣጠልክለት ዲያብሎስም ሆነ የሚጠሉህ ሁሉ ብዙ መጥለፊያ ብልሃቶችን በፊትህ ይዘረጋሉ።

ፈጽሞ ያላልምከው ፈተና ውስጥ ማለፍ ትጀምራለህ። በውስጥህ በርኩሰት፣ በቁሳዊነትና በትዕቢት ከራስህ ጋር እስኪታወቅህ መጋጨት ትጀምራለህ። ነገር ግን ጠላትህን አብዝተህ ስትቃወመው ካንተ እንደሚሸሽ አትዘንጋ።

## ***መንፈስ ቅዱስ እምነት እና ተስፋህን ይጨምራል።***

ለጥቂት ሰዎች ቤተ ክርስቲያን እንደ አማራጭ የመዝናኛና የትወና ሥፍራ ነች። መደበኛ የአምልኮ ሥርዓቶች እንኳ ልማድ እየሆኑ መጥተዋል። “እንደተለመደው በሚቀጥለው እሁድ የተለመደው መደበኛ የአምልኮ ፕሮግራም ይኖረናል።” ብለን የቀጣዩን ሣምንት መርሃ ግብር ማስተዋወቅ ተለምዷል። ሆኖም ግን በቀደመቸው ቤተ ክርስቲያን ዘንድ እንዲህ አልነበረም። በትልቅ ተስፋ ዕለት ዕለት ይሰባሰቡ ነበር። *ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤*

Free digital copy from ServeNow

*በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ* (የሐዋርያት *ሥራ* 2:43)።

በአንዲት ትልቅ ከተማ ውስጥ ያለችን አጥቢያ በመጋቢነት የሚያገለግል አንድ ወዳጅ አለኝ። የማክሰኞ ምሽት የጸሎት መርሃ ግብርን ለመታደም ሰዎች ይሰለፋሉ! ለምን? ምክንያቱም የእግዚአብሔር መገለጥ እምነታቸውን ከፍ አድርጎታል! በዕለት ተዕለት ጉዳያቸው ውስጥ እግዚአብሔርን ጣልቃ ገብነት ተስፋ አድርገው ይመጣሉ፤ ደግሞም አያፍሩም!

መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችሁ ውስጥ እምነትንና ተስፋን እንዲጨምር ፍቀዱለት። በየዕለቱ በቀንም ሆነ በማታ በሕይወታችሁ ውስጥ፣ በቤተ ክርስቲያን በተሰበሰባችሁ ጊዜ ሁሉ መገለጥ ይፈልጋል። እግዚአብሔር ተራና የተለመደ አምላክ አይደለም፤ በፍጹም አይለመድም።

## ***መንፈስ ቅዱስ የተትረፈረፈ ሕይወትን ይሰጣል።***

ኢየሱስ ሲናገር *እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ* (ዮሐንስ 10:10)። አንዳንድ ትርጉሞች ይህንን የተትረፈረፈ ሕይወት ይሉታል። ለተትረፈረፈ መንፈሳዊ ሕይወት፣ ሃብት እና ኃያል ለመሆን አትጨህም? ለእያንዳንዳችን ይህንን ሊያደርግ ይፈልጋል።

ለግምት ከሚያስቸግር ከማናቸውም ነገሮች በላይ የሚያልፍ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ታገኛላችሁ። ድንገት ሰዎች ባንተ ላይ ሲማከሩ ምንም አትጨነቅም። በአንተ ውስጥ ያለው የእርሱ ሕይወት ከውጭ በሚደርስብህ ግፊት በቀላሉ የሚበላሽ አይደለም።

Free digital copy from ServeNow

## መንፈስ ቅዱስን እንዴት ማወቅ እንችላለን?

በሕይወቴ መንፈስ ቅዱስን ለማስተናገድ ምን ያክል ጊዜ አማኝ መሆን አለብኝ? ምናልባት ሰላሳ ወይም ሦስት ዓመታት? ሦስት ሰዓታት ወይስ ሦስት ሴኮንዶች?

በቅድሚያ ያለ መንፈስ ቅዱስ *ሥራ* ድኅነት ራሱ እንደሌለ መረዳት ይኖርብናል። ስለ ኃጢአት እና ፍርድ የሚወቅሰን እርሱ ነው። የመስቀልና ትንሳኤን ወጤት እንድንረዳ አእምሮአችንንና ልባችንን የሚከፍትልን እርሱ ነው። በስርየት ውስጥ ያለው የጸጋ *ሥራ* እውነት የሚሆነው፣ ማለትም ኢየሱስ በእኛ ፈንታ ያለፈውን ኃጢአታችንን ወስዶ ይቅር እንዳለን ብቻ ሳይሆን አሁን ያለንበት ሕይወት እውን የሆነው እና የዘላለምን ተስፋ እንኳ የሰጠን በእርሱ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው።

አንዳንድ የሥነ መለኮት ምሁራን ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ብቸኛው የመንፈስ ቅዱስ *ሥራ* እንደሆነ አጽንዖት ሲሰጡ ሌሎች ደግሞ “ሁለተኛ በረከት” ብለው ይቀበሉታል። በግሌ እግዚአብሔር ከሁለት በላይ በረከቶች አሉት! ቢያንስ 102!

መጽሐፍ ቅዱስ የመንፈስ ቅዱስን *ሥራ* ለዕለተ ድኅነት ብቻ እንደሆነ አድርጎ አይወስነውም። በሐዋርያት *ሥራ* 19 ላይ ጳውሎስ በኤፌሶን የነበሩትን አማኞችን *ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?* ብሎ ጠየቃቸው።

በሐዋርያት *ሥራ* 8 በፊሊጶስ አገልግሎት በሰማርያ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ነበር። በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያትም ለማየት ወደ ሰማርያ ወረዱ። *እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው፤ ከእነርሱ በአንዱ ላይ ስንኳ ገና አልወረደም ነበርና።*

በድኅነት ወቅት ለአማኞች በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ቅጽበታዊ ክስተት ቢሆንም እግዚአብሔር ግን በየጊዜው መንፈስ ቅዱስን ይሞላብናል። በመንፈስ ቅዱስ እንድንሞላ

Free digital copy from ServeNow

ሲያበረታታን፣ ትክክለኛው ትርጉሙ ቀጣይነት ያለውን እንቅስቃሴ ማጉላት ነው።

## *በእምነት እግዚአብሔርን ጠይቀው*

በመንፈስ ቅዱስ ዕለት ዕለት እንዲሞላህ እግዚአብሔርን በእምነት ጠይቅ። ምናልባት አንዳች አለመታዘዝ በሕይወትህ ውስጥ እንዳለች ሕይወትህን ደጋግመህ ፈትሽ። ለምን? ጴጥሮስ በአይሁዳዊያን ሸንጎ ፊት ቆሞ በሐዋርያት ሥራ 5፡32 እንዲህ ብሎ ተናገረ *እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን፣ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው።*

## *ጸልይ*

እግዚአብሔር ስላንተ የገባውን የተስፋ ቃል እንዲፈጽም ጸልይ። ለእግዚአብሔር ኀለዎት በሕይወትህ ውስጥ ምን ያክል ጉጉት አለህ? በሌሊት ወደ ባልንጀራው ሄዶ እንጀራ ካለው እንዲሰጠው የጠየቀውን ሰው ታስታውሳለህ? የለመነውን እስኪሰጠው ድረስ ባልንጀራውን ከመወትወት አልቦዘነም ነበር። ከትንሣኤ በኋላ ኢየሱስ ቢያርግም በአትክልት ሥፍራ ውስጥ የገባላቸውን የተስፋ ቃል እንዲሰጣቸው ደቀ መዛሙርቱ በአንድነት እየጸለዩ ይጠባበቁ ነበር። *አባቴ የሰጣችሁን የተስፋ ቃል እስኪትቀበሉ በኢየሩሳለም ቆዩ።* እግዚአብሔር በሕይወትህ ውስጥ እንዲሠራ እየጸለይህ በተስፋ ጠብቅ።

አንድ ነገር ልጨምርልህ፤ የለመንከው ማንኛውም ነገር በጠበቅህበት መንገድ ላይመጣ ይችላል። እግዚአብሔር ሣንቲም ስንከትበት የፈለግነውን የትኛውንም ጣፋጭ እንደሚሰጠን ማሽን አይደለም።

እርሱ እግዚአብሔር ነው። በሕይወትህ ውስጥ እንደወደደ ይሠራል። መንፈስ ቅዱስም የሆነ አካላዊ እንቅስቃሴ ስላደረግህ ወይም አንዳች ምስጢራዊ ‘ፎርሙላ’ ስላወራህ

Free digital copy from ServeNow

የምትሻውን የሚዘረግፍልህ አይደለም። ነገር መንፈስ ቅዱስ በውስጥህ በመኖሩ ከውስጥ ማንነትህ የሚመነጭ የሕይወት ውኃ ምንጭ ነው። ኢየሱስ ስለ ሕይወት ውኃ ምንጭ ሲናገር ስለ ማን ነበር የተናገረው?

*ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ፤ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና* (ዮሐንስ 7:39)።

## *እግዚአብሔር መልካሙን ሊሰጥህ ይፈልጋል።*

የእግዚአብሔር ፈቃድ መልካሙን ሁሉ ሊሰጥህ ነው። ኢየሱስ ሲናገር *እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፣ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው* (ሉቃስ 11:13)?

ኢየሱስ የተናገረለትና ይህ የተሰጠን ተስፋችን በውስጥህ እርሱ ማን እንደሆነና ምን ማድረግ እንደሚችል ለማወቅ ትልቅ መሻት እንዲኖርህ ጸሎቴ ነው። ምናልባት የቀደሙት አባቶች ባወቁት ማንነት ልክ እውን ሆኖ እኛም ልንቀምሰው እንችል ይሆናል።

## *መንፈስ ቅዱስ ተራ ሰዎችን ይጠቀማል።*

የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን በተራ ወንዶችና ሴቶች ስብስብ የተሞላች ነበር። መሪዎቿ እንኳ ኢየሱስ በተያዘበት ሌሊት በፍርሃት ጥለውት የሄዱ የቀድሞ ዓሣ አጥማጆችና ቀረጥ ሰብሳቢዎች ነበሩ። ደፋሮችና የእምነት ሰዎች እንኳ አልነበሩም። እምነትም ሆነ ድፍረት የሚጎድላቸው በማኅበረሰባቸው ውስጥ በተራነት የሚታወቁ ነበሩ። የክርስትና ሃይማኖት አመራር ለመሆን በምንም ዓይነት ምርጫ ውስጥ የሚገቡ አልነበሩም።

Free digital copy from ServeNow

በሐዋርያት ሥራ 2 መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ እነዚያ ተራ ሰዎች በድንገት ተለወጡ። በእምነት እና በድፍረት ኢየሩሳሌምን ደግሞም ዓለምን በሙሉ ገለባበጧት።

በሥነ መለኮት እውቀታቸው ነው እንዳይባል ምንም ዓይነት ሥልጠና አልወሰዱም። የአዲስ ኪዳን ቅጂዎችን ማከፋፈል አይችሉም ነበር። ምክንያቱም ያኔ ገና አልተጻፈምና። ባለጠጎች ሆነው የዘመነ የድምጽ ማጉያ መሣሪያዎችን በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ እየተጠቀሙ አልነበረም። ድሆች ከመሆናቸውም የተነሣ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ እንኳ አልነበራቸውም።

የአይሁድ እምነት መሪዎች ምንም ያልተማሩና ድሆች እንደነበሩ ስለ ሚያዉቁ ይሳለቁባቸው ነበር። በዙሪያቸው ለነበሩ የፖለቲካ መሪዎችም ጽንፈኛ አክራሪዎችና መጻተኞች ተደርገው ተወሰዱ።

የነበራቸው ብቸኛ ነገር የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነበር። ለየትኛውም ጉዳይ እርሱን እንዲደገፉት ኢየሱስ ነግሯቸዋል። በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩት አማኞች ያለ መንፈስ ቅዱስ ድጋፍ የክርስትና ጎዳና ተስፋ ቢስ መሆኑን ተረድተዋል። የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንም ወደዚህ መረዳት መመለስ አለባት።

Free digital copy from ServeNow

## ለጥናት እና ግብረ መልስ የሚረዱ ጥያቄዎች

- መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?

- ባሕርያቱስ ምንድናቸው?

- በመጽሐፍ ቅዱሳችን መንፈስ ቅዱስ በብዙ ነገሮች ተመስሏል። ጥቂቶቹን ታስታውሳቸዋለህ?

- መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን የሚያደርገው ነገሮች ምንድነው?

- የመንፈስ ፍሬ ምንድነው?

- የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታዎች የትኞቹ ናቸው?

Free digital copy from ServeNow

- በክርስቶስ ስትድን በመንፈሱም ይሞላሃል። ነገር ግን በዚህ መንፈስ ዕለት ዕለት ትሞላለህ?

- ለእግዚአብሔር የተለየ ፍቅር አለህ?

- መንፈስ ቅዱስ የተለዩ ሰዎችን ብቻ ይጠቀማል ወይስ ተራ ሰዎችንም ይጠቀማል?